የመንገድ ትራንስፖርት ረቂቅ አዋጅ ላይ የቀረበ አጭር መግለጫ

ጥር 2014 ዓ.ም

በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር **468/1997** ማሻሻያ ላይ የቀረበ የቀረበ አጭር መግለጫ

1. መግቢያ

የመንገድ ትራንስፖርት ከአንድ አገር ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ ዕድገት ጋር ካለው ጠቀሜታ አንጻር ጎልቶ በመታየቱ በ 1934 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ ስለተሽከርካሪዎች መጻፍ የሚል አዋጅ ቁጥር 11/1934 የወጣ ሲሆን በየጊዜው የመንግስትን አደረጃጀትና አወቃቀር በመከተል እስከ 1997 ዓ.ም ለአምስት ጊዜ ተሻሽሎ አሁን በስራ ላይ ባለው አዋጅ ቁጥር 468/97 ደርሷል።

አሁን ስራ ላይ ያለው አዋጅ ቁጥር 468/1997 እንዲሻሻል ከትራንስፖርት ሚኒስቴር በደብዳቤ ቁጥር 1.2/78 ባዘዘው መሰረት የባለስልጣን መ/ቤቱ የጥናት ቡድን በማቋቋም ጥናት ተደርጓ። በጥናት ቡድኑም ሲፈተሽ አዋጁ አገሪቷ የደረሰችበትን የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ዕድገት ሊሸከም እንደማይችል ከማመላከቱም በላይ በውስጡ ያሉት ድንጋጌዎችም በሌሎች ሕጎች የተሻሩ እና ዘርፉን የሚመራው ተቋም ወቅቱ የሚጠይቀውን ቴክኖሎጂ በመጠቀም የሚታዩት ብልሹ አሰራሮችን በመቅረፍ በሰውና በንብረት ላይ እየደረሰ ያለውን የትራፊክ አደጋ መቅረፍ ባለመቻሉ አዋጁ እንዲሻሻል ጥናታዊ ግኝቱ አመላክቷል።

2. የማሻሻያ አዋጁ አስፈላጊነት

የትራንስፖርት መቆጣጠሪያ አዋጅ ቁጥር 468/1997 በ 1997 ዓ.ም የወጣ እንደመሆኑ መጠን ለአስራ አራት አመት ያገለገለ ሲሆን በዚህ ጊዜ ውስጥ በአገሪቷ እያደገ የመጣው የኢኮኖሚና የማህበራዊ ዕድገት ጋር ሊጣጣም ባለመቻሉ አዋጁን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

3. የረቂቅ አዋጁ ዓላማና ግብ

3.1 የረቂቅ አዋጁ ዓላማ

የመንግድ ትራንስፖርት ቁጥጥርና አገልግሎትን የአገሪቱን ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ዕድገት ጋር እንዲዘምን ዘርፉን በጥናትና ምርምር ጎልብቶ በቴክኖሎጂ የተደገፈ ሆኖ በሰውና በንብረት ላይ የሚደርሰውን የመንገድ ትራፊክ አደጋን እንዲቀንስና የትራንስፖርት አገልግሎቱ እንዲሳለጥ የሚያስችል እንዲሁም በዘርፉ የፌዴራል መንግስት ሥልጣንና ሃላፊነት ከክልል መንግስታት ሥልጣንና ሃላፊነት ጋር በማይጣረዝ መልኩ ረቂቅ አዋጁን ማዘጋጀት ይሆናል።

3.2 የረቂቅ አዋጁ ግብ

የተዘጋጀውን ረቂቅ አዋጅ ከሚመለከተው ባለድርሻ አካል እና የክልል ትራንስፖርት ቢሮዎች ጋር በቅድመ ረቂቅ ዝግጅትና በድህረ ረቂቅ ዝግጅት በኋላ በምክክር በማዳበር ረቂቅ አዋጁን ለሚመለከተው ለሚያጸድቀው የመንግስት አካል ማቅረብ ይሆናል።

4. በረቂቅ አዋጁ ውስጥ የተሻሻሉ አዲስ የተካተቱና በ **468/1997** የነበሩ በረቂቅ አዋጁ እንዳይካተቱ የተደረጉ ድንጋጌዎች ማብራሪያ

4.1 በአዋጁ 468/1997 የነበሩና በረቂቅ አዋጁ እንዳይካተቱ የተደረጉ ድንጋጌዎች

ተ/ቁ	በአዋጅ ቁጥር 468/1997 የነበረው	በረቂቅ አዋጁ እንዳይካተት የተደረገበት ምክንያት
1.	በአዋጁ አንቀጽ 2(33) የሞተር ባቡር ማለት በምድር ባቡር ሐዲድ ላይ የሚንቀሳቀስ ማንኛውም ተሽከርካሪ ነው የሚለው	የባቡር ትራንስፖርት አስተዳደርን በተመለከተ 1048/2009 የሚተዳደርና በአዋጅ ቁጥር 468/1997 የሚፈጸም ተግባር ካለመኖሩ በተጨማሪ በአዋጅ ቁጥር 1048/2009 አንቀጽ 50 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በአዋጅ ቁጥር 468/1997 አንቀጽ 2(3) 3(2) 7(4) እና 23(1) ድንጋጌዎች በመሻራቸው
2.	በአዋጁ አንቀጽ 2(34) ሀዲድ ማለት በኢትዮጵያ መርከብ ወይም በአገር አቋራጭ የውሃ ላይ ማጓጓዝ ላይ ተቀጥሮ ወይም ተመድቦ እንዲሰራ የተደረገ ማንኛውም ሰው ሲሆን አዛዡን ነጂውንና ለማጁን ያጠቃልላል የሚለው	
3.	በአዋጁ አንቀጽ 3 የአፈጻጸም ወሰን በንዑስ አንቀጽ 2 ላይ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ ሀዲዶች አጠቃቀም በሀዲዶች በሚገለገሉ ባቡሮችና ነጂዎች የሚለው	
4.	በአዋጁ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 4 የምድር ባቡር ትራንስፖርትን አስመልክቶ ለባለስልጣኑ የተሰጡት ሀላፊነቶች ሀ. ለባቡር ነጂዎች ፈቃድ መስጠትና ማደስ፣ ለ. ባቡሮችን መመዝገብና የቴክኒክ ምርመራ ማድረግ፣ ሐ. ስለምድር ባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ማውጣት፣ መ. በኢትዮጵያ ውስጥ መንገደኞችና ዕቃዎች በምድር ባቡር ስለሚጓዙበት ሁኔታ ደረጃ ማውጣትና መከታተል፣ ሠ. የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚሰማሩ ሰዎችና ድርጅቶችን መመዝገብ፣ የሙያ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠትና መከታተል፣ ረ. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የባቡር አደጋ ሲከሰት መመርመርና ሪፖርት ማቅረብ፣ ሰ. የባቡሮችን አሰራር ሊኖራቸው የሚገባውን መሳሪያዎች ክብደትና መጠናቸውን እንዲሁም የተሳፋሪን ብዛትና የጭነት ክብደት መወሰን፣ ሸ. ለባቡር መጠገኛ ጋራዥ የብቃት ሰርተፍኬት መስጠት ቀ. የባቡር ተርሚናሎችን ደረጃ ማውጣት በ. በሐዲድ መስመሮችና የዲዛይን ደረጃ ማውጣት	

	ተ. የሐዲድ መስመሮችና የደህንነት መሳሪያዎች የወጣላቸውን መስፈርት ማሟላታቸውን ማረጋገጥ	
5.	በአዋጁ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 5 የውሃ ትራንስፖርትን በተመለከተ ለባለስልጣኑ የተሰጡት ሃላፊነቶች ሀ. በብሐየራዊና ዓለም ዓቀፍ ሕጎች መሰረት I. የኢትዮጵያ መርከቦችንና አገር አቋራጭ የውሃ ላይ መጓጓዎችን መመዝገብና የባህር ጉዞ ብዙነት የምስክር ወረቀት መስጠትና ማደስ II. ለባህረኛ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትና የባህረኛ ደብተር መስጠትና ማደስ III. በኢትዮጵያ መርከቦችና በአገር አቋራጭ የውሃ ላይ መጓጓዣዎች እንዲሁም በመሳሪያዎቻቸው ላይ አስፈላጊውን የቴክኒክ ምርመራ እንዲካሄድ ማድረግ ለ. የባህር ማመላለሻ አደጋ በደረሰ ጊዜ የፍለጋና የማደን ተግባር እንዲካሄድ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ ሐ. የባህረኞች ማሰልጠኛ ተቋማት እንዲቋቋሙ ማበረታታትና በአገሪቱና በዓለም ዓቀፍ ሕጎች መሰረት ደረጃቸውን መወሰን	የማሪታይም ዘርፍ አስተዳደርን በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 549/1999 የሚተዳደርና በአዋጅ ቁጥር 468/1997 የሚፈጸም ተግባር ካለመኖሩም በላይ በአዋጅ ቁጥር 549/1999 አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 2 በአዋጁ ቁጥር 468/1997 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 5 እና 23 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 የተሻሩ ሺሆን እንዲሁም አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 31 እና 35 የመርከብና የባህረኛ ትርጉም በዚህ ረቂቅ አዋጅ ውስጥ ጥቅም ላይ ስላልዋለ እንዲወጣ ተደርጓል።
6.	የአዋጁ አንቀጽ 23 የባህረኛና የባቡር ነጂነት ፈቃዶች 1- ማናቸውም ሰው ከባለስልጣኑ ፈቃድ ካላገኘ በስተቀር ባህረኛ መሆን ወይም በኢትዮጵያ ሀዲዶች ላይ ባቡርን ማሽከርከር አይችልም 2- በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ቢኖርም ከዚህ አዋጅ መጽናት በፊት በሚመለከተው አካል የተሰጠ ፈቃድ በፈቃዱ እስከተመለከተው ጊዜ የጸና ይሆናል።	
7.	በአዋጁ የአፈጻጸም ወሰን አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 3 በኢትዮጵያ መርከቦችና ባህረኞች እንዲሁም በጠቅላላው የየብስና የውሃ ትራንስፖርት ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል የሚለው	
8.	በአዋጁ አንቀጽ 2(31) መርከብ ማለት በሞተር ሃይል የሚንቀሳቀስ የውሃ መጓጓዣ ነው የሚለው	
9.	በአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 35 ባህረኛ ማለት በኢትዮጵያ መርከብ ወይም በአገር አቋራጭ የውሃ ማጓጓዣ ላይ ተቀጥሮ ወይም ተመድቦ እንዲሰራ የተደረገ ማንኛውም ሰው ሲሆን አጓጓዡን ነጂውንና ለማጁን ያጠቃልላል።	
10.	በአዋጁ አንቀጽ 2(8) የመንጃ ፈቃድ ማለት ባለሞተር ተሽከርካሪዎችን ለመንዳት የሚያስችል በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጣ ደንብና መመሪያ መሰረት የሚሰጥ መንጃ ፈቃድ	በአጠቃላይ ከአሽከርካሪ ጋር የተያያዘው እንዳይካተቱ የተደረጉ ድንጋጌዎች በአዋጅ

	ነው የሚለው	ቁጥር 1074/2010 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 10 እና 11 እንዲሁም አንቀጽ 23 የተሸፈኑ በመሆናቸው ነው
11.	በአዋጁ ቁጥር 22 የመንገድ ፈቃድ አስፈላጊነት በሚለው አንቀጽ ሥር ማንኛውም ሰው ዓይነቱ ተለይቶ የተሰጠው የጸና መንገድ ፈቃድ ሳይኖር በመንገድ ላይ ተሽከርካሪ መንዳት እንደሌለበትና የተሽከርካሪ ባለቤት መፍቀድ እንደሌለበት እንደዚሁም በአነዳድ ለመማር የሚቻልበት ባለስልጣኑ መመሪያ እንደሚያወጣ የተደነገገው አልተካተተም	
12.	በአዋጁ አንቀጽ 2(9) የፌዴራል የመንገድ ፈቃድ ማለት በጋራ ጥቅም መርሕ / ሪስፕሮሲቲ/ መሰረት ለውጭ አገር ለሚሄዱ ኢትዮጵያዊያን ባለሞተር ተሽከርካሪ ለማሽከርከር የሚያስችል በዚህ አዋጅ መሰረት የሚሰጥ መንገድ ፈቃድ ነው የሚለው	
13.	የአዲስ አበባ ከተማ የትራንስፖርት ባለስልጣንና የድሬዳዋ ከተማ የትራንስፖርት ጽ/ቤት በአዋጁ ቁጥር 468/1997 ለባለስልጣኑ ተላልፍ የነበሩት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለኮሚሽኑ ተላልፈዋል፤ የኮሚሽኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሆነውም በዚህ አዋጅ እንደተደራጁ ተቆጥረው ስራቸውን ይቀጥላሉ የሚለው።	የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በራሱ ቻርተር በተሰጠው ስልጣንና ሃላፊነት መሰረት የትራንስፖርቱን ዘርፍ የሚመራ ተቋም በመዝርጋቱና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርም በተመሳሳይ ሁኔታ ሊሰራ ስለሚችል።

4.2 በአዋጁ ቁጥር 468/1997 ውስጥ የነበሩ በረቂቅ አዋጁ ማሻሻያ የተደረገው ከእነ ምክንያቱ

ተ/ቁ	በአዋጁ 468/97 የነበረ	በረቂቅ አዋጁ ማሻሻያ የተደረገ	ማሻሻያ የተደረገበት ምክንያት ማብራሪያ
1.	በአዋጁ መግቢያ ላይ በአጠቃላይ ትራንስፖርትን የሚያመላክቱ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚለው ሀረግ	የመንገድ ትራንስፖርትን በሚገልጽ ሁኔታ ተሻሽሏል።	የውሃ እና የባቡር ትራንስፖርት በሌላ ሕግ የተሸፈነ በመሆኑ እና ረቂቅ ሕጉ የመንገድ ትራንስፖርትን ብቻ በሚያመላክት የተዘጋጀ በመሆኑ
2.	አንቀጽ አንድ የትራንስፖርት አዋጁ የሚለው	ብሔራዊ የመንገድ ትራንስፖርት ኮሚሽን በሚል ተሻሽሏል	በፌዴራል ደረጃ የሚሰሩት ሥራዎች አገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ ሥራዎችን ብቻ የሚያመላክት በመሆኑና የመንገድ ላይ ትራንስፖርትን ብቻ ለመግለጽ ነው።
3.	አንቀጽ 2(1) ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ማለት እንደቅደም ተከተሉ የመሰረተ ልማት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው የሚለው	ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ማለት እንደቅደም ተከተሉ የትራንስፖርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው በሚል ተሻሽሏል	በአሁኑ ጊዜ የሚኒስቴሩ ስያሜ ትራንስፖርት ሚኒስቴር በመሆኑ
4.	አንቀጽ 2(2) ማህበር ማለት የሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ	ማህበር ማለት የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ ለተሰማሩ ሰዎችና	1- የሕዝብ የሚለው አብዛኛው ሰው የተረዳው የሕዝብ ማመላለሻን እንጂ የጭነት ማመላለሻ

	ለተሰማሩ ሰዎችና ድርጅቶች የተቋቋመና በዚህ አዋጅ መሰረት የተመዘገበ ማህበር ነው	ድርጅቶች የተቋቋመና በአዋጅ ቁጥር 468/97 እና በዚህ አዋጅ መሰረት የተመዘገበ ማህበር ነው በሚል ተሻሽሏል	ተሸከርካሪዎችን የማይመለከተው አድርጎ በመገንዘባቸው የጭነት እንዲካተት አስተያየት የተሰጠ በመሆኑ 2- አዋጅ ቁጥር 468/97 ሲሻር በአዋጁ መሰረት የተመዘገቡ አካላት ሕጋዊነታቸውን ለማረጋገጥ
5.	አንቀጽ 2(4) የዲስፕሊን መመሪያ ማለት በሚኒስትሩ የወጣ የዲስፕሊን እርምጃ አወሳሰንና አፈጻጸም መመሪያ ነው	አንቀጽ 2(5) የዲስፕሊን መመሪያ ማለት በኮሚሽኑ የወጣ የዲስፕሊን እርምጃ አወሳሰን አፈጻጸም መመሪያ ነው በሚል ተሻሽሏል	ቅድመ ረቂቅ ውይይት ከባለድርሻ አካላት ከባለስልጣኑ ኃላፊዎች ውይይት ሲደረግ የዲስፕሊን መመሪያና በሚኒስትሩ ይውጣ ቢባልም በየጊዜው ተለዋዋጭ በመሆኑ የዲስፕሊን መመሪያው በየጊዜው እየታዬ መሻሻል የሚፈልግ እንደ መሆኑ መጠን ለአሰራሩ አመቺነት በሚኒስትሩ ከሚወጣ በኮሚሽን እንዲወጣ ቢደረግ የተሻለ መሆኑ በውይይት ወቅት የታመነበት በመሆኑ በኮሚሽኑ እንዲወጣ አስተያየት በመቅረቡ ነው
6.	አንቀጽ 2(3) (ለ) የሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ማለት የግል ተብሎ ያልተለመደ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሁሉ ነው	አንቀጽ 2(4)(ለ) የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ማለት ከከተማ ታክሲ በስተቀር የግል ተብሎ ያልተመደበ ማንኛውም የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ነው በሚል ተሻሽሏል	የሕዝብ ተብሎ የተጠቀሰው የጭነትን የማያካትት መሆኑን የታክሲ አገልግሎትን የሚያካትት ስለሚመስል ግልጽ ማድረግ አስፈላጊ ስለሆነ
7.	አንቀጽ 3 የተፈጻሚነት ወሰን ለክልል ቢሮዎች በሕግ የተሰጣቸው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ መንገዶች አጠቃቀም በመንገዶች በሚገለገሉ ተሽከርካሪዎችና አሽከርካሪዎች ተፈጻሚ ይሆናል የሚለው	ለክልል ቢሮዎች በሕግ የተሰጣቸው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ መንገዶች አጠቃቀም በመንገዶች በሚገለገሉ እና ከኢትዮጵያ ጋር የጋራ ስምምነት ባላቸው አገራት በሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎችና አሽከርካሪዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል	ከኢትዮጵያ ውጭ በሚንቀሳቀሱ አሽከርካሪዎችና ተሽከርካሪዎች ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆን ግልጽ ለማድረግ ነው
8.	ክፍል ሁለት ትራንስፖርት ባለስልጣን	ብሔራዊ የመንገድ ትራንስፖርት ኮሚሽን	1- ብሔራዊ የተባለበት ምክንያት በአገር አቋራጭ እና ከኢትዮጵያ ጋር ስምምነት ካላቸውና በዓለም

			ዓቀፍ ደረጃ የሚሰሩ ሥራዎችን ለማመላከት 2- እያደገ የመጣውን ኢኮኖሚና የትራንስፖርት አገልግሎት ፍላጎትን ለማስተናገድና ከጎረቤት አገራት ጋር ከሚደረገው የትራንስፖርት ትስስር አንጻር የበለጠ ለማጠናከር በኮሚሽን ደረጃ መቋቋሙ አስፈላጊ በመሆኑ 3- ኮሚሽን የተመረጠበት ምክንያት በብዙ አገራት ኮሚሽን ሬጉሌት(ቁጥጥር) የማድረግና የኦፕሬሽን ሥራንም የሚሰራ በመሆኑ ነው
9.	በባለስልጣን የሚሉት	ኮሚሽን በሚለው ማሻሻያ ተደርጓል	ከላይ በተራ ቁጥር 8 ከተገለጸው ምክንያት በተጨማሪ ኮሚሽን የተሻለ ቁመና ኖሮት ብልሹ አሰራሮችን መታገልና ማስወገድ እንዲቻል ከአገር ውስጥና ከውጭ አካላት ጋር የሚኖረውን የግንኙነት አግባብ ጠንካራ መሰረት ላይ ለማስቀመጥ ብሎም የጥናትና ምርምር አቅሙን ለማሻሻል እንዲያስችል
10.	አንቀጽ 5 ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንደአስፈላጊነቱ በማንኛውም ሥፍራ ሊያቋቁም ይችላል የሚለው	አንቀጽ 5 በአገር ውስጥ እና በጎረቤት አገር በማንኛውም ስፍራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሊያቋቁም እንደሚችል ተሻሽሏል	የሕግ ድጋፍ ሳይኖር በተግባርም እየተሰራ በመሆኑ እና የተፈጻሚነት ወሰኑም ከሀገር ውጭ ከኢትዮጵያ ስምምነት ካላቸው እና አገር ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪ አሽከርካሪ ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆን ሆኖ የተደነገገ በመሆኑ
11.	አንቀጽ 6(2) የትራንስፖርት አገልግሎት ደህንነቱ የተጠበቀና ምቾት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ	አንቀጽ 6(3) ሆኖ የመንገድ ት/አገልግሎት ደህንነቱ የተጠበቀ ከተፈጥሮ አካባቢ ጋር የሚስማማ ምቾት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ	አገልግሎቱ የመንገድ ትራንስፖርትን ብቻ በመሆኑ እና ከተፈጥሮ የአየር ንብረት ጋር ምቹነቱን ማረጋገጥ አስፈላጊ ስለሆነ
12.	አንቀጽ 6(4) ትራንስፖርት በማንኛውም ረገድ እንዲያድግ ማበረታታት	6(5) የመንገድ ትራንስፖርት በማንኛውም ረገድ እንዲያድግ ዘርፉን በጥናት ምርምር መደገፍ መበረታታትና መመቻቸት	በመንገድ ትራንስፖርት ላይ ያተኮረ ጥናትና ምርምር በማካሄድ ለውጥ ማምጣት እንደሚያስፈልግ ለማሳየት
13.	አንቀጽ 7 የባለስልጣኑ ሥልጣንና ተግባር ሥር በትራንስፖርት፣ በመንገድ	የባቡርና የውሃ ትራንስፖርት ድንጋጌዎች እንዲወጡ ተደርጎ በመንገድ ትራንስፖርት	በመንገድ ትራፊክ ደህንነት ዙሪያ የሚፈጸሙ ተግባራት በግልጽ ተለይቶ እንዲቀመጥና ኮሚሽኑ

	ትራንስፖርት በምድር ባቡር ላይና በውሃ ትራንስፖርት ላይ የሚለው	አገልግሎት አሰጣጥና በጥናትና ምርምር ላይ ያተኮረ ማሻሻያ ተሰርቷል	አገልግሎት የሚሰጥባቸውን ለይቶ በማስቀመጥ እንዲሁም የጥናት ምርምር ሥራንም እንዲያካትት በማስፈለጉ ነው
14.	ከአንቀጽ 8 ጀምሮ ዋና ሥራ አስኪያጅ እና ባለስልጣን የሚሉት	አንቀጽ 8 ጀምሮ ያሉት ኮሚሽነር እና ኮሚሽን በሚል ተሻሽሏል	ተቋሙ በኮሚሽን ደረጃ እንዲቋቋም ረቂቅ አዋጅ በመቅረቡ
15.	አንቀጽ 14 ስለማህበራት መቋቋም የሚለው	ስለትራንስፖርት ማህበራት /ድርጅት መቋቋም	ኮሚሽኑ ማህበራትን ብቻ ሳይሆን በንግድ ሕግ የተቋቋሙትን የትራንስፖርት ድርጅቶችን ስለሚከታተል
16.	አንቀጽ 15(3) ባለስልጣኑ የማህበርን ምዝገባ የማይቀበል ከሆነ በ 7 ቀናት ውስጥ ማስታወቅ ይገባዋል	ኮሚሽኑ የማህበሩን /የድርጅቱን/ የምዝገባ ጥያቄ የማይቀበል ከሆነ በ 10 ቀናት ውስጥ ማስታወቅ እንዳለበት ተሻሽሏል	በተግባር እንደሚታየው ውስብስብ ጉዳዮችን መርምሮና ገምግሞ በ 7 ቀናት ውስጥ መልስ ለመስጠት ጊዜ ስለሚያጥር
17.	አንቀጽ 16(1) የማህበራት የዕድሳት ጊዜ ከመስከረም 1 ቀን እስከ የካቲት 30 መሆኑን ይደነግጋል	አንቀጽ 16(1) የማህበር የድርጅት የዕድሳት ጊዜ ከሐምሌ 1 እስከ ታህሳስ 30 ቀን ድረስ እንዲሆን ተሻሽሏል	ከንግድ ሕግ ጋር ተመሳሳይ እንዲሆን ታስቦ ነው፣ የ 6 ወራት ጊዜያት በቂ እንደሚሆን በመታሰቡ ነው
18.	አንቀጽ 18(2) መረጃን ማስተላለፍ ያለበት አካላት ከትራንስፖርት ጋር የተያያዙ አስፈላጊውን መረጃ በወቅቱ ማቅረብና ማስተላለፍ እንዳለባቸው ይደነግጋል	መረጃን ማስተላለፍ ያለባቸው አካላት በተዘረጋው የቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ለኮሚሽኑ፣ ለክልሉ ወይም ከተማ መስተዳድሩ ማቅረብ ወይም ማስተላለፍ እንዳለባቸው ተሻሽሏል	በአዋጁ ላይ ለማን ማስተላለፍ እንዳለባቸው ግልጽ ካለማድረጉም በላይ ለክልላቸው /ከተማ አስተዳደራቸው ውሳኔ ለመስጠት አመቺ ስለማይሆንና የሪፖርት ግልጽነት ለመፍጠር
19.			
20.			
21.			
22.			
23.			
24.			
25.			
26.			

4.3 በአዋጅ ቁጥር 468/97 ያልነበሩና በረቂቅ አዋጁ እንደ አዲስ የተካተቱ ድንጋጌዎች

ተ/ቁ	በረቂቁ አዲስ የተካተቱ ድንጋጌዎች	አዲስ እንዲካተቱ የተደረገበት ምክንያት

1.	አንቀጽ 2(3) ድርጅት ማለት የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ ለተሰማሩ ሰዎች በንግድ ሕግ መሰረት የተቋቋመ እና በአዋጅ ቁጥር 468/97 እንዲሁም በዚህ አዋጅ የተመዘገቡ ድርጅት ነው	በተግባር በአክሲዮን ወይም ኃ/የተ/የግ/ማህበር በመንገድ ትራንስፖርት ዘርፍ ተደራጅቶ እና ተመዝግበው ሥራ እየሰሩ በመሆናቸው
2.	አንቀጽ 2(4) ተቋም በዘርፉ የተሰማሩ በዚህ አዋጅ በአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ አዋጅ በተሽከርካሪ መለያ መመርመሪያ እና መመዝገቢያ አዋጅ ቁጥጥርና ክትትል የሚደረግባቸው መንግስታዊ የሆኑና መንግስታዊ ያልሆኑ ናቸው	አዋጁ በሌሎች አዋጅ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የሚቆጣጠራቸው ተቋማትን በግልጽ ለማስቀመጥ
3.	በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 2(31)(32) ልዩ ስልጠና እና መደበኛ ስልጠና ልዩነታቸው ምን እንደሆነ በትርጉም ክፍል ተተርጉሟል	ልዩ ስልጠና እንደተሃድሶና ልዩ ባለሙያዎችን ለማፍራት እንዲቻል በረቂቁ በመግለጽ ከመደበኛ ሥልጠና ልዩነቱን ለማስቀመጥ ነው
4.	በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 2(33) እና (34) ኮሚሽንና ብሔራዊን በትርጉም ክፍል እንደ አዲስ ተካቷል	በማሻሻው ላይ ባለስልጣን የሚለው ኮሚሽን በሚል የቀረበ በመሆኑ ብሔራዊ ምን ማለት እንደሆነ በግልጽ ለማስቀመጥ ነው
5.	በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 2(35) ትራንዚት ፈቃድ ማለት ኢትዮጵያ ስምምነት ካላት አገራት ጋር በሚደረግ የመንገድ ትራንስፖርት ትስስር ለአሽከርካሪና ተሽከርካሪ የሚሰጥ ፈቃድ ነው	በኮሚሽኑ የሚሰጠው የትራንዚት ፈቃድ አገልግሎት በግልጽ ለማስቀመጥ
6.	በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 5(2) የመንገድ ትራንስፖርት ኢንስቲትዩት በዚህ አዋጅ ተጠሪነቱ ለኮሚሽኑ ሆኖ የጥናትና የምርምር ማዕከል ሆኖ ይደራጃል የሚል አዲስ አንቀጽ ገብቷል።	የምርምር እና ጥናት ኢንስቲትዩት ራሱን ችሎ እንዲቋቋም በአገኘነው መድረክ የተሰጠ አስተያየት ተቀባይነት በማግኘቱ
7.	በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 6 ዓላማዎች ሥር በንዑስ አንቀጽ 2 የመንገድ ትራንስፖርትን የሚመለከቱ ማናቸውም መረጃዎችን በመሰብሰብ ማጠናቀር የሚል አዲስ አንቀጽ ተካቷል	በዘርፉ ያለውን የመረጃ ክፍተት ለመዝጋት ዓላማ ተደርጎ ሊሰራ ስለሚገባ
8.	በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 7(1/ለ) ደኅንነቱ የተረጋገጠ፣	የትራንስፖርት አገልግሎት ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ልዩ ድጋፍ የሚሹ አካላትን

	ከተፈጥሮ አካከባቢ ተስማሚየሆነ፣ ቀልጣፋ፣ የተሟላ፣ የተመጣጠነ እና ልዩ ድጋፍ ለሚፈልጉ ዜጎች ምቹ የሆነ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት መኖሩን መከታተል እና ማረጋገጥ፤ የሚል እንደ አዲስ ገብቷል	ያማከለ መሆኑና ከአካባቢ የአየርና የተፈጥሮ ሁኔታ ጋር ተስማሚ መሆናቸውን በማረጋገጥ ረገድ አዋጁ ክፍተት ስለነበረው በዚህ ረቂቅ አዋጅ ላይ በግልጽ ለመደንገግ አስፈላጊ በመሆኑ
9.	በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 7(1/ተ) ብሔራዊ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች የሚያስከፍሉትን ታሪፍ በገበያ መር ፖሊሲ ለሚሰጡት አገልግሎት ማግኘት ለሚገባቸው ትርፍ ግምት ውስጥ በማስገባት ማፅደቅ፤ የሚለው እንደ አዲስ ገብቷል	ድርጅቶች በንግድ ሕግ የሚተዳደሩ በመሆኑ በንግድ ተደራጅቶ ወደ ዘርፉ የሚገቡት በገበያ መር በውድድሩ ሕብረተሰቡ የሚፈልገውን አማራጭ የማግኘት ዕድሉን ስለሚያሰፋፋለት እንደ አዲስ እንዲገባ ተደርጓል።
10.	ከመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጥጥ ጋር በተያያዘ በማናቸውም አካል መካከል አለመግባባት እና ክርክር ሲፈጠር ባለጉዳዮቹ ሲጠይቁ በአግባቡ አይቶ መወሰን እንዳለበት በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 7 የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባር ሥር በንዑስ አንቀጽ 1 ሥር በፊደል ተራ ጎ ላይ እንደ አዲስ ገብቷል	በትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ክልል ከክልል ጋር ማህበር /ድርጅት/ ከማህበር/ድርጅት ጋር ያለመግባባት ችግሮች ሲከሰቱ በአጭር ጊዜ ኮሚሽኑ መፍትሔ መፈለግና መስጠት ስላለበት ነው።
11.	በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 7(1/ነ) የመካከለኛ ትራንስፖርት መገልገያ መሣሪያዎች ከአገሪቷ ጅግራፊያዊ አቀማመጥ ጋር በሚጣጣም እና ለተጠቃሚው በሚያመች መልኩ እንዲሰፋፉ ማበረታታት፤ የሚለው እንደ አዲስ ገብቷል	ማንኛውም የትራንስፖርት አገልግሎት እንደ አገሪቱ ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ ሁኔታ ተስማሚ የሆነ የትራንስፖርት አገልግሎት ለማስፋፋትና ለማበረታታት ታስቦ የገባ አንቀጽ ነው
12.	በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 7(1/ኘ) በማኅበር ተደራጅተው ወደ ድርጅት የሚሸጋገሩ ማኅበራት ያፈሩት ንብረት የሚሸጋገርበትን ዝርዝር ሁኔታ ለመንግሥት ማቅረብ፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ማድረግ፤	ማህበራት ወደ ድርጅት ሲሸጋገሩ ያፈሩትን ንብረት በሚመለከት ውሳኔ የሚሰጥ ወይም የውሳኔ ሀሳብ የሚያቀርብ አካል ባለመኖሩ ማህበራት ወደ ንግድ ድርጅት ሲሸጋገሩ የማህበራት ንብረት ለብክነት እንዳይዳርግ በማሰብ ነው

13.	በመንገድ ትራንስፖርት አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችና አሰራሮች በአገር ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውሉ እንዲስፋፉእንዲዳብሩ በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 1 በፊደል ተራ ቁጥር ዠ ላይ በተጠቀሰው አንቀጽ እና ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ የ ላይም የተሽከርካሪዎች ፓርኪንግና መናኸሪያዎችን ከግል ባለሀብቱ ጋር ኮሚሽኑ እንዲያስፋፋና እንደሚያስተዳድር ይደነግጋል።	እነዚህ አንቀጾች ከመንገድ ደህንነት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች በቴክኖሎጂ የተደገፉና ከግል ባለሀብቱ ጋር ተሳስሮ መስራትን ግልጽ አድርጎ ማስቀመጥ አስፈላጊ በመሆኑ
14.	በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 7(1/ጀ) በኮሚሽኑ ወይም በክልል ቢሮዎች በሚመዘገቡ ተሽከርካሪዎች ላይ የሚለጠፍ ሠሌዳ መሥፈርት በማውጣት እንዲመረት ማድረግ፤ ስርጭታቸውን መከታተል፤ አገልግሎታቸውን የጨረሱ ሰሌዳዎች እና ባለቤታቸው ጠፍቶ ብዙ ጊዜ የቆሙ ተሽከርካሪዎችየሚሰበሰቡበትንና የሚወገዱበትን መመሪያ ማውጣት፤ የሚለው እንደ አዲስ ገብቷል	በአዋጁ ላይ ያልነበረና በተግባር በሥራ ላይ ችግር ሲያጋጥሙ መፍትሔ ለመስጠት ላይ ሕግ ድጋፍ በባለመኖሩ አስቸጋሪ ሆኖ በመቆየቱ እንደ አዲስ አንቀጽ ገብቷል
15.	በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 7(1/ገ) ተግባርና ኃላፊነቱን በአግባቡ ለመፈፀም እንዲቻለው ተቆጣጣሪዎችን በቋሚነትም ሆነ በጊዜያዊነት በማንኛውም የኢትዮጵያ ክልል ውስጥ መመደብ፤ የሚለው እንደ አዲስ ገብቷል	የፌዴራል ተቆጣጣሪዎች ከክልልና ከፖሊሲ ተቆጣጣሪዎች ጋር በቅንጅት ለማስተባበር ሲመደቡ በአዋጅ 468/1997 ላይ በግልጽ ባለመደንገጉ የፌዴራል መንግስት ሥልጣን የለውም የሚል ጥያቄ በማስነሳቱ ነው እንደ አዲስ የገባው
16.	በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 7(1/ጠ) የዘርፉንና የህብረተሰቡን ደኅንነት የሚጎዳ ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ለሚፈፀመው ድርጊት በማንኛውም አካል ላይ ተገቢው ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ፤ የሚለው እንደ አዲስ ገብቷል	በዘርፉ ላይ የሚፈጸመው ሕብረተሰቡን የሚጎጉ ድርጊቶች ሕጋዊ እርምጃ የሚያስወስድ አካል በግልጽ ሊቀመጥ ስለሚገባ
17.	በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 7(1/ጨ) በዘርፉ የወጡ ሕጎችን እና ስታንዳርዶችን በመተግበር ረገድ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡና ሙስናንም በመታገል ረገድ ጥሩ ውጤት ያስገኙ ክልሎችን፣ ተቋማትን፣ ማኅበራትን፣ ድርጅቶችን	በዘርፉ የተንሰራፋው ብልሹ አሰራር ከመታገል በተጨማሪ ከብልሹ አሰራር በአንጻራዊ የተሻሉ አካላትን በመለየት እውቅና በመስጠት ሙስናን መታገል ተገቢ በመሆኑ

	ወይም ሰዎችን ለሽልማት የሚበቁበትን መስፈርት እና የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት በሚኒስቴሩ ሲፀድቅ ተግባራዊ ማድረግ፤ የሚለው እንደ አዲስ ገብቷል	
18.	በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 7(1/ጰ) የመንገድ ትራንስፖርት ዘርፍ ፖሊሲዎችን፣ ህጎችን፣ ስታንዳርዶችን እና እቅዶችን አተገባበር ሰንሰለቱን በጠበቀ መልኩ የመምራት፣ የመከታተል እና የመቆጣጠር፤	የዘርፉን ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ስታንዳርዶችና ዕቅዶች እንደ አገር የማስፈጸም የመከታተልና የመምራትና እና የመቆጣጠር ሚና ለኮሚሽኑ በግልጽ ሊሰጠው ስለሚገባ
19.	በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 7(1/ፈ) ማንኛውም የመንገድ፣ የባቡር፣ የሕንፃ መሠረተ-ልማት ግንባታዎች ከመከናወናቸው በፊት የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎትን እና የመንገድ ትራፊክ ደኅንነትን ታሳቢ ያደረገ መሆኑን መከታተልና ማረጋገጥ፤	በመንገድ ትራንስፖርት ዘርፍ አንዱና ዋነኛው ተግዳሮት የግንባታዎች ዲዛይንና የመሰረተ ልማት ግንባታዎች ክፍተት በመሆኑ እነዚህ ተግባራት ሲከናወኑ የመንገድ ትራንስፖርት ዘርፍ መከታተል ማወቅና የራሱን አስተዋጽዎ ማድረግ ስላለበት ነው
20.	በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 7(2/ረ) በዘርፉ ግልፅነትና ተጠያቂነትን መሠረት በማድረግ ፍትሐዊ፣ ቀልጣፋ፣ ተደራሽ ጥራት ያለውና በቴክኖሎጂ የተደገፈ ዘመናዊ አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ፤ እና	በዘርፉ ያለው የፍትሐዊነት ቀልጣፋነትና ተደራሽነት መጓደል በቴክኖሎጂ ተደግፎ መለወጥ ስላለበት
21.	በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 7(2/ሰ) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የማበረታቻ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን በዘርፉ የተሰማሩ ድርጅቶችና ተቋማትን በመለየት ለሚመለከተው የመንግሥት አካል ማቅረብ፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ማድረግ፤	ዘርፉን ለማዘመን እና ወደ ተሻለ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ማሻሻል እንዲቻል በዘርፉ የተሰማሩ ድርጅቶችና ተቋማትን መንግስት የሚበረታቱበት ሁኔታ እንዲፈጠር በተለያዩ መድረኮች ሀሳብ የተነሳ በመሆኑ በረቂቅ አዋጁ ውስጥ እንዲካተቱ ስለታመነበት ነው
22.	በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 7(3/ሀ) የመንገድ ትራንስፖርትን እና የትራፊክ ዳህንነትን የሚመለከቱ ማናቸውም የክፍተት መረጃዎችንና ስታትስቲኮችን በቋሚ ሁኔታ በመተንተን ክፍተቱን በሥልጠና መሙላት፤	በዚህ ረቂቅ አዋጅ የመረጃ ክፍተቶችን በመለየትና በመተንተን እንዲሁም ክፍተቱንም በሥልጠና መሙላት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በረቂቁ ላይ እንደ አዲስ እንዲካተት ተደርጓል
23.	በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 7(3/ለ) የትራንስፖርት አገልግሎት እና የመንገድ ትራፊክ ዳኅንነት በሚመለከት ልዩ፣ መደበኛ እና አጫጭር ሥልጠናዎችን መስጠት፤	በዘርፉ ከተለመደው ሥልጠናዎች በተጨማሪ ልዩ ስልጠናዎች መደበኛና አጫጭር ሥልጠናዎች ተለይቶና በመርህ ግብር በመያዝ ስልጠና እና የምክር አገልግሎቶች መስጠት በማስፈለጉ
24.	በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 7(3/መ) የክልል ትራንስፖርት ቢሮዎችን እና የዘርፉን ባለድርሻ አካላትን የአቅም ክፍተትን በጥናት በመለየት ችግሩን ለመፍታት የሚያስችል የአቅም	

	ግንባታ መርሀግብር መንደፍና መተግበር፤	
25.	በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 7(3/ሠ) ከመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ጋር በተያያዘ የምክር አገልግሎት መስጠት፤	
26.	በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 7(3/ረ) በኢንስቱትዩቱ የሚሰጠው አገልግሎት ግልፅ፣ ፍትሐዊ፣ የተጠያቂነት መርህን የተከተለ እንዲሆን እና ከብልሹ አሰራር የፀዳ እንዲሆን አስፈላጊውን ጥረት ማድረግ፤	ኢንስቲትዩቱ ሲደራጅ ከብልሹ አሰራር የጸዳና ሕጋዊ አገልግሎት እንዲሰጠው ለማስደረግ ነው
27.	በመንግስት የሚሾሙ ም/ኮሚሽነሮችን እንደሚኖሩ በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ ገብቷል	በ 2006 ዓ.ም በባለስልጣኑ የመዋቅር ጥናት አስፈላጊነቱ ታምኖበት በተግባር ተፈቅዶ ም/ዋና ዳይሬክተሮች እየሰሩ በመሆኑ ነው
28.	የምክትል ኮሚሽነሮች ሥልጣንና ተግባር እንደ አዲስ ገብቷል	ም/ኮሚሽነሮች ሃላፊነታቸውና ተግባራቸው በሕግ መደገፍ ስላለበት

5. ቅድመ ማርቀቅ ምክክርና ድህረ ማርቀቅ ምክክር በተመለከተ

4.1 ቅድመ ማርቀቅ ምክክርን በተመለከተ

ረቂቅ አዋጁ ከማዘጋጀት በፊት የተቋሙ የበላይ ሃላፊ ከተቋሙ የሚኔጅመንት አባላት ጋር በመመካከር 6 አባላት ያሉት የጥናት ቡድን አቋቁቀሞ ጥናት ቡድኑም በመመካከር የጥናት ሰነድ ከማዘጋጀቱ በፊት ከበላይ ሃላፊ እና ከሚኔጅመንት አባላት ጋር በመመካከር እንዲሁም ጥናት ቡድኑ በሶስት ንዑሳን ቡድኖች በመከፋፈል ከትራንስፖርት ዘርፍ ፣ ከአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት ፣ ከተሽከርካሪ ምርመራ ተቋም፣ ከተሽከርካሪ አስመጪዎች፣ ከባለጋራዦች እንዲሁም ከምሁራንና ከሕግ ባለሙያዎች ጋር ምክክር በማድረግ በሁሉም የምክክር ወቅት የአዋጅ ማሻሻል አስፈላጊነት ታምኖበታል።

4.2 የድህረ ማርቀቅ ምክክር በተመለከተ

1. በ 03/03/2011 ዓ.ም ከተቋሙ ኃላፊዎች እና ቡድን መሪዎች ጋር ውይይት ተደርጓል።

2. በ 05/04/2011 ከክልልና ከተማ አስተዳደር የመጡ የክልል ትራንስፖርት ቢሮ ሃላፊዎች፤ ከተሽከርካሪ ቴክኒክ ምርመራ ተቋማት እና ከአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት ጋር ውይይት ተደርጓል።
3. በ 22/04/2011 ዓ.ም ከትራንስፖርት ማህበራት ጋር ውይይት ተደርጓል።
4. በ 17/05/2011 ዓ.ም በአዳማ ከተማ ከክልል ትራንስፖርት ቢሮ ሃላፊዎችና ባለሙያዎች ጋር ውይይት ተደርጓል።
5. በ 18/06/2011 ዓ.ም ከትራንስፖርት ሚኒስትር ዴኤታዎች እና የሚኒስትር መ/ቤት ሃላፊዎች በተገኙበት ውይይት ተካሂዷል።
6. በ 03/07/2011 ዓ.ም በድጋሚ ከትራንስፖርት ማህበራት ጋር ውይይት ተደርጓል።
7. በ 13/07/2011 ከፌዴራል የተለያዩ የመንግስት ተቋማት ከተወጣጡ ሃላፊዎችና ባለሙያዎች ጋር ውይይት ተደርጓል።

4.3 በውይይቱ የተነሱ ዋና ዋና ነጥቦች

1. የውጭ አገር ተሞክሮ ላይ በጥናቱ የተካተቱት የተመረጡበት ምክንያት ማብራሪያ ስለመጠየቁ
2. በሕገ መንግስቱ የተቀመጡት የፌዴራል ሥልጣንና ተግባር ከጥናቱ አኳያ የተፈተሸ ስለመሆኑ
3. ከባለድርሻና ክልሎች ጋር በሰፊው ውይይት ስለማድረጉና ግበዓት ስለመሰብሰቡ
4. ኮሚሽን የተባለበት ምክንያት እንዲብራራ ተጠይቋል
5. ከሰሌዳ ምርት ገቢ እንደምናገኝና ማስወገድም እንደምንችል በረቂቁ ቢገባ
6. የቴክሎጂ አጠቃቀምን በተመለከተ በደንቡ ቢካተት
7. በትራንስፖርት ሚኒስቴር መመሪያ እንደሚያወጣ በረቂቅ አዋጁ ቢካተት
8. ባለስልጣን የነበረው በኮሚሽን ደረጃ ሲዋቀር በዘርፉ ያለውን ብልሹ አሰራሮችን የመቆጣጠርና እርምጃ የመውሰድ ጉዳይ ጠንከር ተደርጎ ቢካተት
9. ከአየር ንብረት ጋር በተያያዘ አዋጁ ማስቀመጥ ያለበት ድንጋጌ ቢካተት
10. የማህበራት ዓላማ እና ምዝገባም ቢፈተሽና ቢጠናከር
11. የግል ባለሀብቱ ተሳትፎ ሊያሳድግ የሚያስችል አንቀጽ ቢገባ
12. የትራንስፖርት ካውንስል አስፈላጊነትና

1. አለመግባባት ሲፈጠር ኮሚሽኑ ውሳኔ መስጠት እንደሚችል እና ሌሎች የኤዲቶሪያልና የረቂቅ አዋጅ ዝግጅት ደረጃው የጠበቀ ቢሆን የሚሉት ዋና ዋና ነጥቦች አስተያየት ቀርቧል።

4.4 የቀረቡት አስተያየቶች እንደግባነታቸው ተወስዶ አብዛኛዎቹ በረቂቅ አዋጁ ላይ የተካተቱ ሲሆን በረቂቅ አዋጁ ላይ ያልተካተቱ ሀሳቦች እንደጥያቄው እንደሚከተለው ማብራሪያ ተሰጥቶባችኋል።

1. የውጪ ተሞክሮ የተወሰደባቸው አገሮችም የፌዴራል ስርዓት የሚከተሉና በዕድገት ደረጃም ከኢትዮጵያ ጋር ተቀራራቢነት ያላቸው ሆኖ አገራቱም አውስትራሊያ፣ ካናዳ፣ ናይጀሪያ፣ ኬንያ፣ ደቡብ አፍሪካ ባንግላዴሽ ህንድና ብራዚል ሲሆኑ የተመዘኑበትም በሕገ መንግስታቸው ላይ የመንገድ ትራንስፖርትን የተመለከቱ ድንጋጌዎች የተካተቱ

መሆኑን አለመሆኑን፣ አደረጃጀታቸው፣ ስያሜያቸው እና ለፌዴራል እና ለክልል መንግስታት የተሰጡ ሃላፊነቶች ከአገራችን ጋር በማነጻጸር የተመረጡ ስለመሆኑ ማብራሪያ ተሰጥቷል፤

2. የትራንስፖርት ማህበራት ካውንስል አስመልክቶ ለተነሳው ጥያቄ የትራንስፖርት አሰሪዎች ፌዴሬሽን በሚል በሠራተኛና ማህበራዊ ሚኒስቴር የተቋቋሙ በመሆኑ እና በጋራ የሚያነሱት ጉዳይ ካላቸው በፌዴሬሽኑ በኩል እየተስተናገዱ በመሆኑ የትራንስፖርት ካውንስል ማቋቋምን ጠቀሜታ ባለመታየቱ በረቂቅ አዋጁ ላይ እንዲካተት አልተደረገም
3. ሕገ መንግስቱም ጋር በማይቃረን መልኩ ረቂቅ አዋጁ የተዘጋጀ ስለ መሆኑም ማብራሪያ ተሰጥቷል።
4. ኮሚሽንና ብሔራዊ የተባለበትም ምክንያት በተደጋጋሚ ጥያቄ በመነሳቱ በዚሁ ሰንጠረዥ ገጽ 8 ተራ ቁጥር 8 በተገለጸው መሰረት ማብራርያ ተሰጥቶባችኋል።

4.4 ማጠቃለያ፡-

አዋጅ ቁጥር 468/1997 ብዙ ዘመናትን ያስቀጠረ እና በሌሎች አዋጆች የተሻሩ ድንጋጋዎች አካቶ የያዘ በመሆኑ መሻሻል ያለበት መሆኑ በሁሉም ባለድርሻ አካላት ዘንድ ታምኖበታል። ረቂቅ አዋጁን ለማዘጋጀት የተለያዩ አገራት ተሞክሮዎችን ለማገናዘብ የተቻለ ከመሆኑም በላይ የትራንስፖርት ማህበራት የሥልጠናና የተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ማዕከላት፣ ክልሎችና የፌዴራል መ/ቤቶች ባለድርሻ አካላት እንዲወያዩበትና ግብዓት እንዲሰጡበት ተደርጓል። የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ትራንስፖርት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተጠሪነት ጉዳይም በዝርዝር ተገምግሞ እልባት እንዲቀመጥ ተደርጎ ረቂቅ አዋጁ የባለሀብቱ ተሳትፎ ለማሳደግ የሚያስችሉ የለውጥ ሀሳቦችን መነሻ በማድረግ የተቀረጸ፣ እያደገ የመጣው የሕብረተሰብ ማህበራዊ እንቅስቃሴና የኢኮኖሚ እድገቱን ሊሸከም በሚያስችል አግባብ ተደራጅቷል። የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን በማሳደግ ደህንነቱ የተጠበቀና ቀልጣፋ አገልግሎት ለማረጋገጥ በሚያስችል አግባብ ታይቷል። በአፍሪካ ቀንድ የሚታሰበው የኢኮኖሚ፣ ውህደት ለማምጣት የሚያስችል የትራንስፖርት ትስስር እንዲኖር ረቂቅ አዋጁ አጋዥ ሚና እንዲኖረው ተደርጎ ቀርቧል።aa